የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶችና በምርጫ ተግባራት ላይ ሰላምና ጸጥታ የሚያስከብሩ የጸጥታ አስከባሪ አካላት የአሠራር ሥርዓት እና የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 12/2013

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### አንቀጽ 1. አውጪው ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 11 እና አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እንዲሁም በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 163 ንኡስ አንቀፅ (2) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

### አንቀጽ 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የምርጫ ጸጥታ አስከባሪ አካላት መመሪያ ቁጥር 12/2013"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው፡፡
2. **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
3. **"የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች (ተቋማት)"** ማለት በየደረጃው ለሚካሄዱ ምርጫዎች የመራጭ እና የእጩዎች ምዝገባ የሚካሄድባቸው፣ መራጮች ድምጽ የሚሰጡበት፣ የድምጽ ቆጠራ፥ ማዳመር እና ውጤት ይፋ የሚደረግባቸው በታዎች ሲሆኑ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ የምርጫ ክልል ፅ/ቤቶች፣ ምርጫ ጣቢያዎች፣ የዞን የማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች እንዲሁም ማንኛውም

የቦርዱ መደበኛ ሥራዎች የሚከናወንባቸውን ተቋማት እና የቦርዱ የምርጫ ቁሳቁስ ማከማቻ መጋዘኖችና የምርጫ ቁሳቁስ ማሰራጫ ቦታዎችንም ይጨምራል፡፡

4. "**የጸጥታ አካላት**" ማለት በመራጮች ምዝገባ እና በድምጽ መስጠት እንዲሁም በሌሎች የምርጫ ሂደቶች የምርጫ ጣቢያዎችን ጨምሮ በምርጫ ማስፈፀሚያ አደረጃጀቶች ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ አግባብነት ባላቸው የፌዴራል እና የክልል ህጎች መሰረት በተቋቋሙ የፌደራል መንግስት፣ የክልል እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የጸጥታ አስከባሪ ተቋማት የሚመደቡ የተቋሙ አባላት ናቸው፡፡

5. **"የጤና መመሪያ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ወቅት የኮቪድ 19 ሥርጭትን ለመቀነስ ያወጣውመመሪያ ቁጥር 9/2013 ነው፡፡

6. **"የምርጫ ተግባራት"** ማለት የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና ቁጥጥር፣የመራጮች ምዝገባ፣ የእጩዎች ምዝገባ፣ የምረጡኝ ቅስቀሳ፣ የመገናኛ ብዙኃን ተደራሽነት፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረገውን የገንዘብ ድጎማ ማከፋፈል፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል ዕጩዎች የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም፣ ለምርጫ የሚያስፈልጉ የምርጫ ጣቢያዎችን ቁጥር መወሰን፣ ድምጽ መስጠትና ቆጠራ፣ ድምጽ አደማመርና ውጤት አገላለጽ፣ የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ እና የቅሬታ አፈታት ሥነ-ሥርዓት፣ የምርጫ ቁሳቁሶችና ሰነዶች ዝግጅት፣ ስርጭትና ጥበቃ፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ፣ ሥልጠናና ምደባ፣ የምርጫ ታዛቢዎች ፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ሥርዓት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል ዕጩዎች ወኪሎች እና ጋዜጠኞች ፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር፣ የመራጮች ትምህርት አሰጣጥና የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ተቋማትና ድርጅቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ሥርዓት ማዘጋጀት፣ ለምርጫ ተግባራት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ይፋ ማድረግ፣ በምርጫ ጉዳዮች ላይ ለባለድርሻ አካላት ሥልጠና ማዘጋጀት፣ በቦርዱ እውቅና ሌሎች የምርጫ ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸው የምርጫ ተግባራት፣ እንዲሁም ሌሎች ከምርጫ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ለቦርዱ በህግ የተሰጡ ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

7. **"ክልል"** ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47/1/ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል አዲስ አበባን እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡

8. የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በአዋጁ ላይ የተሰጠ የቃላት ትርጉም ለዚህ መመሪያም ያገለግላል፡፡

**አንቀጽ 4. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በሁሉም የምርጫ ሂደቶች ላይ በቦርዱ የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች የየዕለት ሥራ እንዲሁም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑበት ሂደት ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር በህግ እውቅና በተሰጣቸው የፀጥታ አካላት በሚመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አንቀፅ 5. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንዱ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሌላኛውንም ፆታ ያካትታል።

**አንቀጽ 6. ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በሁሉም የምርጫ አደረጃጀቶች እና ተግባራት ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር የሚመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎችን የአሰራር ሥርዓትና ሥነ-ምግባር መወሰን ነው።

## ክፍል ሁለት

## በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች እና የምርጫ ተግባራት ላይ የሚመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎች ተግባራት

**አንቀጽ 7. ዋና ዋና ተግባራት**

በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶችና ተግባራት ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ የሚመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎች የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናሉ።

1. በሁሉም የምርጫ ተግባራት ላይ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶችና አካባቢያቸው ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ፣
2. የተመዝጋቢዎችንና የመራጮችን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ፣
3. የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑበት ወቅት በሴቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል፣ ተፈጽሞ ሲገኝም በወቅቱ ለሚመለከተው ተቋም ሪፖርት ማድረግና፣ ፈጻሚውንም ለህግ ማቅረብ፣
4. በምርጫ ወቅት የጸጥታ ችግር በሚጋጥም ጊዜ የምርጫ አስፈጻሚዎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ የምርጫ ታዛቢዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩዎችን እና ወኪሎቻቸውን፣ ጋዜጠኞችና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ፣ ለሴቶችና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ትኩረት መስጠት፣

5. በሁሉም የምርጫ ሂደት በጉዞ ወይም በሥርጭት ላይ ያሉ፣ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ እንዲሁም ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ የምርጫ ቁሳቁሶችና ሰነዶችን ደህንነት መጠበቅ፣
6. የቦርዱን መመሪያዎች በመጣስ ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች ለመግባት የሚሞክሩ ሰዎች ሲኖሩ ከቦርዱ ሰራተኞች ወይም ምርጫ አስፈፃሚዎች በሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ መሰረት እንዳይገቡ ማድረግ።
7. የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶቸን የበላይ ኃላፊዎች ህጋዊ ትዕዛዝ የማያከብሩ ሰዎች ከምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማቱ የስራ ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ መውጣታቸው አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቱ ኃላፊ በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት ትዕዛዝ ለመፈፀም እምቢተኛ የሆኑትን ግለሰቦች እንዲወጡ ማድረግ፣
8. በሕግ መሰረት በመራጭነት ለመመዝገብ ወይም ለመምረጥ ብቁ ያልሆነ ሰው ወይም ለመመዝገብ ወይም ለመምረጥ መብት ለሌለው ሰው ድጋፍ ሰጪ ሆኖ የመጣ ረዳትን ከምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋሙ እንዲወጣ ለማድረግ ከምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋሙ ኃላፊ የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብላቸው በጥያቄው መሰረት እንዲወጣ ማድረግ፣
9. ከቦርዱ ፍቃድ ያላገኘ ወኪል፣ የምርጫ ታዛቢ፣ ወይም ጋዜጠኛ ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋሙ እንዳይገባ ማድረግ ሲያስፈልግ ከምርጫ ማስፈፀሚያ ተቋሙ ኃላፊ በሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ መሰረት ግለሰቦቹን እንዳይገቡ መከልከል፣
10. ወደ ምርጫ አደረጃጀቶች የሚገቡ ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው ወኪሎች፣ ታዛቢዎች፣ ጋዜጠኞች እና ቅሬታ ያላቸው ባለጉዳዮች ቦርዱ ያወጣውን የጤና መመሪያ ባለማክበራቸው ከአደረጃጀቱ ማስወጣት አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ከምርጫ አደረጃጀቶቹ ሀላፊ በሚቀርብ በመሰረት ግለሰቦቹን እንዲወጡ ማድረግ፣
11. በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች(ተቋማት) ውስጥ ወይም በአካባቢያቸው ወንጀል ሲፈጽም የተገኘ ወይም ለመፈጸም የተዘጋጀ ሰው መኖሩን በተጨባጭ ሲረዱ ወይም ከህብረተሰቡ ጥቆማ ሲደርሳቸው የተጠረጠረውን ሰው በህግ አግባብ ይዞ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣
12. ከምርጫ አስፈጻሚዎች በሚቀርብላቸው የትብብር ጥያቄ መሰረት ተመዝጋቢዎች ወይም መራጮች ወደ ምርጫ ጣቢያ ሲገቡ የሰልፍ ተራቸውንና አካላዊ ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲገቡ ማድረግ፣ ከምርጫ ማስፈፀሚያ ተቋሙ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ጋር በመተባበር ማስፈፀሚያ አደረጃጀቱ የተመሰረተበትን ቦታ ምቹነት ከግምት ውስጥ ባሥገባ ሁኔታ በተቻለ መጠን ሴቶች፣ አቅመ ደካሞችና አረጋውያን በተለየ ሰልፍ እንዲስተናገዱ ማድረግ፣

13. የምርጫ ቁሳቁሶችና ሰነዶች እንዲሁም የምርጫ ሰራተኞች በዕቅድም ሆነ በድንገት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን ጥበቃ ማድረግ፣

14. ከምርጫ ጣቢያ ወደ ምርጫ ክልል ወይም ወደ ቦርዱ ቅ/ፍ ጽ/ቤት ወይም ወደ ቦርዱ ዋና መስሪያ ቤትየሚወሰዱ የምርጫ ቁሳቁሶች ወይም ሰነዶች ሲኖሩ አስፈላጊውን ጥበቃና እጀባ ማድረግ።

15. አግባብነት ባላቸው የቦርዱ መመሪያዎች ላይ የተዘረዘሩ ሌሎች የጸጥታ ማስከበር ተግባራትን እንዲያከናውኑ ከቦርዱ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ማከናወን ናቸው።

## አንቀጽ 8. ግዴታውን መወጣት የማይችል የጸጥታ አስከባሪ

1. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ ከላይ በአንቀጽ 7 ሥር የተዘረዘሩትን ተግባራት እያከናወነ ባለበት ጊዜ ድንገትኛ የህመም ሥሜት ወይም ምልክት ከተሰማውና ግዴታውን ለመወጣት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር ተገቢውን የጤና መመሪያ መከተል እንዲሁም በመጣበት ተቋም የአስራር ስርዓት መሰረት ሥለ ህመሙ ለመደበው ተቋም ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።
2. የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም) ኃላፊ ይህንን የአሰራር ስርዓትና የሥነ ምግባር መመሪያ የጣሰ ወይም ኃላፊነቱን የማይወጣ የጸጥታ አስከባሪ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ ለጸጥታ አስከባሪው የቅርብ አለቃ ማሳወቅ አለበት። በተጨማሪም ለሚመለከተው የቦርዱ ጽ/ቤት ሥለ ሁኔታው ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።
3. የሚመለከተው የጸጥታ ተቋም ከላይ በንዑስ ቁጥር 2 መሰረት ማሳወቂያ እንደደረሰው በተቻለ ፍጥነት በተቋሙ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት ሌላ የጸጥታ አስከባሪ እንዲተካ ያደርጋል።

## ክፍል ሶስት

## <u>የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶችና የምርጫ ተግባራት ጸጥታ አስከባሪዎች የአሰራር ሥርዓት እና የሀይል አጠቃቀም</u>

## አንቀጽ 9. የጸጥታ አስከባሪዎች የአሰራር ስርዓት

1. የጸጥታ አስከባሪዎች ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት የሚሰማሩት ቦርዱ ከሚመለከተው የጸጥታ ተቋም ጋር በሚያደርገው ውይይትና የጸጥታ ተቋሙ በሚያደርገው ምደባ መሰረት ብቻ ነው።

በተቋሙ የሚደረገው ምደባም በተቻለ መጠን ሴት የጸጥታ አስከባሪዎችን ያካተተ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል።

2. ለእያንዳንዱ የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም እና የምርጫ ተግባር የሚመደበው የጸጥታ አስከባሪ ቁጥር እንደየ አካባቢው ተጨባጭ የጸጥታ ሁኔታ እና ቦርዱ ከሚመለከተው የጸጥታ ተቋም ጋር በሚያደርገው የምደባ ዕቅድ ላይ ተመስርቶ ይሆናል።
3. በጸጥታ አስከባሪነት በምርጫ ጣቢያዎች ላይ የሚመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎች የመራጮች ምዝገባ ወይም ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ ቢያንስ ከአንድ ቀን በፊት በተመደቡበት የምርጫ ጣቢያ ተገኝተው አስፈላጊውን ፍተሻ ማድረግና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማስተካከል አለባቸው።
4. በዚህና ሌሎች ቦርዱ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶቹ ሥለሚያከናውኗቸው ዝርዝር ተግባራት ከሚመድባቸው ተቋም ወይም እንደ ሁኔታው ከቦርዱ ተገቢው ማብራሪያ ሊሰጣቸው ይችላል።
5. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ ወደ ተመደበበት ቦታ ሲመጣ የመደበውን የጸጥታ አስከባሪ ተቋም መለዮ (ዩኒፎርም) መልበስ ይኖርበታል።
6. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ ከተመደበበት የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም ወደ ሌላ ምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም) ሊቀየር የሚችለው በመደበው ተቋም መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ብቻ ነው። ቅያሪው ወይም ዝውውሩ ለዚሁ ጉዳይ በቦርዱ በተዘጋጀ መመዝገቢያ ሰነድ ወይም በቃለ ጉባኤ እንዲሁም በሚመለከተው የጸጥታ ተቋም የመመዝገቢያ ሥርዓት ላይ ሊመዘገብ ይገባል።
7. ማንኛውም የጸጥታ አሥከባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ኃላፊ ጥሪ ካልተደረገለት በስተቀር ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋሙ) መግባት የለበትም።
8. በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም)ወይም በአካባቢው እና የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች የተመደቡ የጸጥታ አስከባሪዎች ኃላፊ በተመደቡበት ቦታ ስለሚከሰቱ አንዳንድ ሁኔታዎች አስፈላጊና ዋና ዋና መረጃዎች በተቋማቸው መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት መመዝገብ ይኖርባቸዋል።
9. በተቋማቸው መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጫ ሳጥን ወይም ቁሳቁስ ይዘው መምጣት ይኖርባቸዋል።

10. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም) ተመድቦ በሚሰራባቸው ጊዜያት ሁሉ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል(ማስክ) ወይም ሌላ አፍና አፍንጫ በአግባቡ የሚሸፈን መሸፈኛ ማድረግን ጨምሮ የጤና መመሪያውን መተግበር ይኖርበታል።
11. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት(ተቋም)ተመድቦ ሲሰራ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ወይም ባጅ ሊይዝና አስፈላጊ ሆኖ በምርጫ አስፈጻሚዎች ሲጠየቅም ማሳየት አለበት።
12. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ጣቢያው ፍተሻ በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ የጤና መመሪያውን ባከበረ መልኩ መሆን አለበት። ፍተሻ የሚደረገውም በተመሳሳይ ጾታ መሆን አለበት።
13. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት ወይም በአካባቢው ድንገተኛ የጸጥታ ችግር ሲያጋጥም ለአካል ጉዳተኞች፣አቅመ ደካሞች፣ሴቶች፣ህጻናትና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለየ ትኩረት በሰጠ መልኩ ጸጥታ የማስከበር ተግባሩን ማከናወን አለበት።

## አንቀጽ 10. የጸጥታ አስከባሪዎች የሀይል አጠቃቀም

በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች (ተቋማት) እና የምርጫ ተግባራት በሚከናወንባቸው ስፍራዎች ሰላምና ደህንነት እንዲያስከብሩ የተመደቡ የጸጥታ አካላት ፀጥታ አስከባሪዎች፡-

1. ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) የስራ ማከናወኛ ቦታ ሊገቡ የሚችሉት በሚመለከተው የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም የሥራ ባልደረባ ወይም ኃላፊ የእርዳታ ጥያቄ ወይም ጥሪ ሲደረግላቸው ብቻ ነው። ይሁን እንጂ በሰዎች ህይወት ወይም አካል ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል፣ ወይም የቦርዱን ወይም የሰዎችን ሀብትና ንብረት ውድመት ሊያስከትል የሚችል በግልጽ የሚታይና የማይቀር ከፍተኛ አደጋ ሲኖር ፍቃድ ወይም ጥያቄ ሳይቀርብላቸው ወደ ምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም የስራ ማከናወኛ ቦታ መግባት ይችላሉ።
2. ከአቅማቸው በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ወዲያውኑ ለምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋሙ ኃላፊና ለራሳቸው የቅርብ አለቃ ማሳወቅ አለባቸው።
3. አስገዳጅ ሁኔታ መፈጠሩ የተላለፈለት የጸጥታ አስከባሪዎቹ የበላይ ኃላፊም በተቻለ ፍጥነት ለችግሩ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

4. የጦር መሳሪያ ወይም ሀይል መጠቀም የሚቻለው የመጣውን ጥቃት ወይም አደጋ ከሀይል ወይም ከጦር መሳሪያ ውጪ በሌላ ማናቸውም መንገድ ማስቀረት ወይም ማስወገድ ያልተቻለና ብቸኛ አማራጭ እንደሆነ ብቻ ነው። የሚወሰደው እርምጃም ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል።
5. ከላይ በንዑስ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥም የሚመለከተው የጸጥታ ተቋሙ የበላይ አካል ወይም ችግሩ በተከሰተበት ቦታ ያለው የበላይ አዛዥ እንደአግባብነቱና እንደ ችግሩ ክብደት ሀይል ወይም የጦር መሳሪያ እንዲጠቀሙ ሊያዝ ይችላል። ከሚመለከትው የበላይ አዛዥ ትዕዛዝ ወይም ፍቃድ ሳይሰጥ ምንም አይነት ሀይልም ሆነ የጦር መሳሪያ መጠቀም አይቻልም።
6. በምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት ውስጥ ወይም አካባቢ በማንኛውም ሁኔታ ተመጣጣኝ ያልሆነ ወይም ከመጠን ያለፈ ሀይል መጠቀም የተከለከለ ነው።
7. ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ የሚወስደው የኃይል እርምጃ ተመጣጣኝና ምክንያታዊ ካልሆነ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የሚያስጠይቀው መሆኑን መረዳትና ማወቅ ይኖርበታል።
8. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 4 የተመለከተውን ሁኔታን ወይም ችግሩን የፈጠረውን አካል ለማስቆም በጸጥታ አስከባሪዎቹ የሚወሰደው እርምጃ እንደቆመ፡-

    ሀ) በሰዎች ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ካለ በፍጥነት የህክምና ድጋፍ ጥሪ ማድረግ እንዲሁም እንደ ጉዳታቸው ደረጃ በቅደም ተከተል እርዳታ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

    ለ) በተቋማቸው መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ሥለ ጉዳዩ ዝርዝር መረጃና ሥለደረሰው ጉዳት አጠቃላይ መረጃ መያዝ ይኖርባቸዋል።

    ሐ) የተፈጠረውን ችግር በአካባቢው ለሚገኝ ለሚመለከተው የጸጥታ አካል በተቻለ ፍጥነት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው። አጠቃላይ ሁኔታውም በቃለ ጉባኤ ወይም በመዝገብ ላይ መመዝገብ ይኖርበታል።

    መ) በተፈጠረው ችግር ምክንያት የደረሰው ጉዳት፣ የወደመ ወይም የጠፋ ንብረት፣ እንዲሁም ችግሩን በፈጠረው አካል ቁጥጥር ሥር ተይዞ ያለ የጸጥታ አሥከባሪ ካለ ሁለም ሊመዘገብ ይገባል።

9. ከላይ በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 መሰረት ኃይል መጠቀም የሚቻለው፡-

    ሀ) በምርጫማስፈጸሚያ ተቋሙ ውስጥ ወይም አካባቢ ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች በግልጽ የሚታይና የማይቀር በራስ፣ ወይም በሌላ ባልደረባ፣ የምርጫ ሰራተኛ፣ ወይም ሌላ ሰው፣ ወይም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ውስጥ የምርጫ ተግባር ለማከናወን የመጡ ተመዝጋቢዎችን፣ መራጮችን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን፣ የፓርቲ ወይም የግል ዕጩዎችና ወኪሎችን፣ ታዛቢዎችን፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትን፣ ወይም

ለተለያየ የምርጫ ሥራ በምርጫ ማስፈፀሚያ አደረጃጀቶች የተገኙ ሰዎችን ህይወትና አካል ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ግልፅ ሥጋት ሲኖርና የተቃጣን ጥቃት ወይም አደጋ ለመከላከል፣

ለ) የምርጫ ቁሳቁሶችንና ሰነዶችን ከመጥፋትና ከውድመት ለመከላከል፣

ሐ) ማንኛውንም የቦርዱን ወይም የመንግስትን ንብረት ከሥርቆት ወይም ከውድመት ለማዳን፣

10. ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች የተመደበ የጸጥታ አስከባሪ ሀይልን በቅጣት መልክ መጠቀም አይችልም።

## አንቀፅ 11. በወንጀል ድርጊት የተጠረጠረ ሰው የአያያዝ ሁኔታ

1. ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ውስጥ ወይም አካባቢ ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ሰላምና ደህንነት እንዲጠብቅ የተመደበ የጸጥታ አስከባሪ በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሲይዝ (በቁጥጥር ሥር ሲያውል) ተገቢውን ህግና የጸጥታ ተቋሙን መደበኛ የአሰራር ሥርዓት ተከትሎ መሆን አለበት።
2. በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋሙ) ውስጥ ወይም አካባቢ ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ሥለ ተከሰተው አጠቃላይ ሁኔታ፣ሥለተወሰደው እርምጃ፣ ሥለተወሰደው እርምጃ አግባብነትና እርምጃውን ለመውሰድ ያሥገደዱ ሁኔታዎችን የያዝ ዝርዝር ሪፖርት ለሚመለከተው አካልና ለቦርዱ ወዲያውኑ በዕለቱ ወይም እጅግ ቢዘገይ በሁለት ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል።

## ክፍል አራት

## <u>በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም)ና በምርጫ ሂደቶች የሚመደቡ የሰላምና ጸጥታ አስከባሪዎች ሥነምግባሮች</u>

## አንቀጽ 12. ትዕዛዞችን ማክበርና ማስከበር

1. በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች የተመደበ ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ ከምርጫ ማስፈፀሚያ አደረጃጀቱ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ጸጥታ የማስከበር ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት።

2. በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች የተመደበ ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ ከበላይ አዛዡ የሚተላለፍለትን ህጋዊ ትዕዛዝ የማክበርና የማሥከበር ግዴታ አለበት።
3. ከሌሎቹ የሞያ ባልደረቦቹና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮና ተግባብቶ መስራት ይኖርበታል።

## አንቀፅ 13. ሙያዊ ሥነ-ምግባርና መልካም ጠባይ ስለማሳየት

በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች የተመደበ ማንኛውም የጸጥታ አስከባሪ፡-

1. የሙያ ሥነ ምግባሩን ማክበርና መጠበቅ አለበት።
2. ከታች በአንቀጽ 15 በተመለከተው መልኩ በገለልተኝነት መስራት አለበት።
3. በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ውስጥ ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ለሁሉም ሰው መልካም ሥነ ምግባር ማሳየት አለበት። ሰዎችን ሲያነጋግሩም በትዕግስትና በቅንነት መሆን ይኖርበታል። እንዲያከናውን የተጠራበትን ተግባር አከናውኖ እንደጨረሰም ከተቋሙ ውስጥ መውጣት አለበት።
4. ምንም አይነት ዘርን፣ ጾታን፣ ሀይማኖትን፣ ቀለምን፣ ወይም ሌሎች ማናቸውንም ሁኔታዎች መሰረት ያደረገ መድሎ ማድረግ የለበትም።
5. በተመደበበት ቦታ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሰዎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር ይኖርበታል።
6. በመራጭነት ለመመዝገብ፣ ድምጽ ለመስጠት፣ ወይም ሌላ የምርጫ ተግባር ለማከናወን የሚመጣውን ህዝብ ትኩረት የሚስብና የሥነ ልቦና ጫና ሊፈጥር የሚችል የተለየ እንቅስቃሴ ከማድረግ መቆጠብ ይኖርበታል።

## አንቀጽ 14. ምክር ስላለመስጠት

ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ፡-

1. ለምርጫ አስፈፃሚዎች ከኃላፊነታቸው ጋር የተያያዘ መመሪያ ወይም ምክር መስጠት አይችልም፣
2. መራጮች ማንንና እንዴት መምረጥ እንዳለባቸው ምክር ከመስጠት መቆጠብ ይኖርበታል።

## አንቀፅ 15. ገለልተኛ ስለመሆን

ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ፡-

1. ተግባራቱን ከወገንተኝነት በፀዳ አኳኋን ማከናወንና ከማንኛውም አካል ወይም ሰው ጋር በማንኛውም ሁኔታ ገለልተኝነቱን ከሚጎዳ ወይም ወገንተኝነትን ከሚያሳይ እንቅስቃሴ መቆጠብ አለበት።
2. በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ውስጥም ሆነ በአካባቢው ማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩን ከመደገፍ ወይም ከመንቀፍ መቆጠብ፤ ከባለስልጣናት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከእጩ ተወዳዳሪዎችና ወኪሎቻቸው፣ ከመራጮችና ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዘ ወይም አወዛጋቢ በሆነ የምርጫ ጉዳይ ላይ ወገንተኝነትን ከማሳየት ወይም ከመግለጽ መታቀብ አለበት።
3. የማንኛውንም በምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለ የፖለቲካ ድርጅትን ወይም እጩን፣ ማንኛውንም አይነት ምልክት ወይም የቅስቀሳ ቁሳቁስ እንደሁኔታው በማሳየት፣ በመያዝ፣ በማስቀመጥ፣ በመስቀል፣ በመለጠፍ ወይም በመልበስና በመሳሰለው ሁኔታ በምርጫ ጣቢያው እንዲሁም ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች መንቀሳቀስ የለበትም።

## አንቀጽ 16. የምርጫን ሚስጥራዊነት እና የመራጮችን መብት ስለማክበር

ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ፡-

1. መራጩ ድምፁን ለማን እንደሰጠ ወይም ማንን እንደሚመርጥ መጠየቅ አይችልም።
2. መራጭ ድምፅ በሚስጢር የሚሰጥበት ክፍል ወይም ለዚሁ የተከለለ ቦታ፣ ወይም በምርጫ ህጎች መሰረት መግባት የተከለከለባቸው ቦታዎች መግባት አይችልም።

## አንቀፅ 17. ጥቅም አለመቀበል ወይም አለመስጠት

1. ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ ከማንኛውም በምርጫ እንቅስቃሴ ከሚሳተፍ የፖለቲካ ድርጅት፣ እጩ፣ የእጩ ወኪል፣ ደጋፊ ወይም ሌላ ማናቸውም ግንኙነት ካለው ግለሰብ ወይም አካል በምርጫ ሂደት ማንኛውንም ተግባር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ወይም በደጋፊነት ለመንቀሳቀስ በማሰብ ጥቅም መቀበል ወይም መስጠት፣ ለመቀበል ወይም ለመስጠት መዋዋል ወይም ቃል መግባት የለበትም ።

2. ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ በመደበው ተቋም ከሚመደብለት ወይም በተለየ አስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት ከሚፈቀድለት መኪና በስተቀር የሌላ ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የደጋፊዎች፣ የዕጩ ተዋዳዳሪዎችን ወይም የግለሰቦችን ተሽከርካሪዎች ለመንቀሳቀሻነት መጠቀም አይችልም።

**አንቀፅ 18. ቅንነት**

1. ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ የተጣለበትን ኃላፊነት የሚወጣበት ሂደት ቅንነት የተሞላበት ሥነ ምግባር ሊኖረው ይገባል።
2. የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥመው ጉዳዩን ወዲያውኑ ለበላይ አዛዡና ለሚመለከተው የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋም ኃላፊ በጸጥታ ተቋሙ መደበኛ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ማሳወቅ አለበት።

**አንቀጽ 19. ስለምርጫው ውጤት አስተያየት አለመስጠት**

ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ የምርጫ ውጤት አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ ምንም አይነት አስተያየት ከመስጠት መቆጠብ ይኖርበታል።

**ክፍል አምስት**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**አንቀጽ 20. ተጠያቂነትና ቅጣት**

1. ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ በዚህ መመሪያና በአዋጁ መሰረት የመተባበር ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ሊያውቅ ይገባል።
2. ማንኛውም በምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀት (ተቋም) ወይም የምርጫ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ተመድቦ ሥራውን የሚያከናውን የጸጥታ አስከባሪ ከበላይ አዛዡ ፍቃድ ሳይሰጠው፣ ወይም ፍቃድ ተሰጥቶትም ቢሆንም ተመጣጣኝ ያልሆነ እርምጃ የወሰደ

እንደሆነ፣ የጦር መሳሪያ ተጠቅሞ እንደሆነ፣ወይም የወሰደው እርምጃ ምክንያታዊ ያልሆነ እንደሆነ በሚመለከተው አካል አግባብነት ባለው ህግ እርምጃ እንደሚወሰድበት ማወቅ ይኖርበታል።

3. በዚህ መመሪያና በሌሎች ህጎች የተጣለበትን ግዴታ ጥሶ የተገኘ የጸጥታ አስከባሪ ሲኖር ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ቦርዱ ለሚመለከተው ተቋም ያሳውቃል።

## አንቀጽ 21. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች እና አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር ይህ መመሪያ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

## አንቀጽ 22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከጸደቀበት ከየካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ